መልእክት ሦስት

## ኤልሳዕ በሕይወት በሆነ ጸጋ አገልግሎቱ
## እና እንደ እግዚአብሔር ሰው
## በባህሪው እንደ እግዚአብሔር ወኪል በመመላለስ
## የክርስቶስ ምሳሌ መሆኑ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- 2 ነገ. 2፡19-22፤ 4፡1—6፡7

**I. ኤልሳዕ በሕይወት በሆነ ጸጋ ተዓምራት በማድረግ የክርስቶስ ምሳሌ ነው—2 ነገ. 4፡9፤ ሉቃ. 4፡27፡-**

ሀ. በብሉይ ኪዳን ላሉት ምሳሌዎች እና ስዕሎች መፈጸም፣ ክርስቶስ እውነተኛው ኤልሳዕ ነው፤ እንደ እውነተኛው ኤልሳዕ፣ ጌታ ኢየሱስ ጣፋጭ እና ደስ የሚያሰኝ ነቢይ፣ የበረከት ነቢይ ነው—2 ነገ. 4፡9፤ ሉቃ. 4፡27፤ 7፡11-17።

ለ. ኤልሳዕ በጸጋ የሆነውን የእግዚአብሔርን አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ የወከለ በብሉይ ኪዳን ያለ ምሳሌ ነው፡-

1. ጸጋ እግዚአብሔር ራሱን እንደ ድሰታችን ለእኛ በመስጠት ሁሉንም ነገር ለእኛ ሲያደርግልን ነው—ዮሐ. 1፡1፣ 14-17።
2. ይህ ጸጋ እኛን ከክርስቶስ ጋር አብረን የምንነግሥ እስከሚያደረግበት መጠን ድረስ የበለጠገውን እና ከፍተኛውን መለኮታዊ ሕይወት ያፈራል—ሮሜ 5፡17።

ሐ. በኢያሪኮ የነበረውን ውኃ በመፈወስ በኤልሳዕ የተደረገው ተዓምር እና ውኃን ወደ የወይን ጠጅ በመለወጥ በጌታ ኢየሱስ የተደረገው ተዓምር ትርጉም አንድ አይነት ነው—ሞትን ወደ ሕይወት መለወጥ—2 ነገ. 2፡4፣ 19፡22፤ ዮሐ. 2፡1-11።

መ. ኤልሳዕ የሌሎችን ነገሮች እንዳሉ አድርጎ መጥራቱ ጌታ ኢየሱስ ሕዝቡን ሲመግብ ካደረገው ነገር ጋር በመርህ አንድ አይነት ነገር ነበር—2 ነገ. 4፡1-7፣ 8-17፣ 42-44፤ ማቴ. 14፡14-21፤ 15፡32-39።

ሠ. ኤልሳዕ የሞተውን ከሞት ማስነሣቱ፣ ለሞተው ሕይወት መስጠቱ፣ ጌታ ኢየሱስ በአካል እና በመንፈስ ካደረገው ነገር ጋር አንድ አይነት ነው—2 ነገ. 4፡18-37፤ ሉቃ. 7፡11-17፤ ዮሐ. 11፡41-44፤ 5፡25።

ረ. ኤልሳዕ የበረሀውን ቅል መርዝ በዱቄት ማምከኑ ጌታ ኢየሱስ በራሱ እንደ ዱቄቱ ደቀ መዛሙርቱን ከፈሪሳውያን እርሾ ከመፈወሱ ጋር በመርህ አንድ አይነት ነው—2 ነገ. 4፡41፤ ማቴ. 16፡12።

ሰ. ኤልሳዕ ውኃ ውስጥ የወደቀውን የምሳር ብረት በእንጨት እንዲንሳፈፍ ማድረጉ የሚያመለክተው ወደ ሞት ውኃ ውስጥ ወድቆ የጠፋውን የኃጢአተኞች ኃይል ክርስቶስ በትንሣኤ በመስቀሉ በኩል መመለሱን ነው—2 ነገ. 6፡6፤ ኤፌ. 2፡1-6።

ሸ. ኤልሳዕ ለሌሎች መለኮታዊ ፈውስን አድርጓል፣ እርሱ ራሱ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ በተዓምር አልተፈወሰም፤ ይህ የጳውሎስ እና የአብሮ ሠራተኞቹ ልምምድ ነበር—2 ነገ. 13፡14፡-

1. ጳውሎስ የፈውስ ጸሎትን ሳያደርግ ጥሮፊሞስን ታሞ በሚሊጢን ተወው፣ ጢሞቴዎስንም ከሆድ በሽታው ለመፈወስ የፈውስ ስጦታውን አልተጠቀመም—2 ጢሞ. 4፡20፤ 1 ጢሞ. 5፡23፤ ሐዋ. 19፡11-12።
2. ጳውሎስ እና አብሮ-ሠራተኞቹ በዚያን በመከራ ጊዜ በውስጡ ሕይወት ቅጣት ሥር እንጂ በውጫዊ ስጦታ ኃይል ሥር አልነበሩም፡-

   ሀ. የቀደመው በሕይወት የሆነ ጸጋ ጉዳይ ነው፤ ኋለኛው በኃይል የሆነ ስጦታ—የተዓምራዊ ስጦታ—ጉዳይ ነው።

   ለ. በቤተ ክርስቲያን ውድቀት እና አንድ ሰው ስለ ቤተ ክርስቲያን መከራ በሚቀበልበት ጊዜ፣ በሕይወት የሆነ ጸጋን ያህል የኃይል ስጦታ አያስፈልግም—2 ጢሞ. 4፡22።

ቀ. ኤልሳዕ በሰውነቱ ሞቶ የነበረ ቢሆንም ከሙታን መካከል አንዱን ሕያው ለማድረግ በመንፈስ ያገለግል ነበር—2 ነገ. 13፡21፡-

1. የሞተው ኤልሳዕ እንኳን ሳይቀር ሰዎችን ሕያዋን ማድረግ ችሎ ነበር።
2. ይህ በትንሣኤ ያለው ክርስቶስ ስዕል ነው—ዮሐ. 11፡25፤ ሐዋ. 2፡24፤ ፊልጵ. 3፡10፡-

   ሀ. እርሱን የነካው ሁሉ ሕያው ይሆን ነበር።

   ለ. ዳግም መወለድ አንድ በመንፈስ የሞተ ሰው የሞተውን እና ከሞት የተነሣውን ክርስቶስ መንካቱን እና ሕያው መሆኑን ያካትታል—ተዛ. ዮሐ. 5፡25፤ ኤፌ. 2፡1-6።

**II. እንደ ሙሴ፣ ሳሙኤል እና ጳውሎስ፣ የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ በምድር ላይ እንዳለ እንደ የእግዚአብሔር ወኪል ተመላለሰ—2 ነገ. 4፡9፡-**

ሀ. ያሕዌ ለፈርኦን አምላክ እንዳደረገው ለሙሴ ነገረው—ዘጸ. 7፥1፦

1. እግዚአብሔር የሚወክለው እና ፈቃዱን የሚያስፈጽም ሰው በሙሴ አግኝቷል፤ ሙሴ ሁልጊዜ ጌታ እንዲል የነገረውን ተናገረ እንጂ በራሱ ፈርኦንን አንዳች ነገር ተናግሮ አያውቅም—3፥16-18፤ 5፥1።
2. በእውነቱ፣ ፈርኦን የእግዚአብሔር አምባሳደር የሆነውን ሙሴን እየሰማ እና ከእርሱ ጋር እየተነጋገረ አልነበረም፤ እግዚአብሔርን እየሰማ እና ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ነበር።

ለ. ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ሕዝብ በምድር ላይ ለመግዛት የእግዚአብሔር ወኪል ነበር፤ እንዲህ እንዳለው ሰው፣ ሳሙኤል የእግዚአብሔር ወኪል ነበር—1 ሳሙ. 1፥11፤ 2፥35፤ 7፥3፤ 8፥22፦

1. ሳሙኤል የእግዚአብሔር ወኪል መሆን የቻለው ማንነቱ እና የእግዚአብሔር ልብ አንድ ስለነበሩ ነው—2፥35፦
   ሀ. እርሱ በእግዚአብሔር ልብ መሠረት የሆነ ሰው ነበር፤ ማለትም፣ እርሱ የእግዚአብሔር ልብ ቅጂ፣ ብዜት ነበር።
   ለ. የሳሙኤል ኑሮ እና ሥራ በእግዚአብሔር ልብ ለነበረ ማንኛውም ነገር መከናወን ነበር።
2. ሳሙኤል የእግዚአብሔር ንግግር እና የእግዚአብሔር አስተዳደር ነበር፣ ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ወኪል ነበር።

ሐ. የእግዚአብሔር ሰው ጳውሎስ በአገልግሎቱ አማኞችን በማጽናናት፣ በእግዚአብሔር ቅንነት በመመላለስ፣ የእግዚአብሔርን ቅንዓት በመግለጥ እና የማስታረቅን አገልግሎት ለማከናወን የክርስቶስ አምባሳደር በመሆን የእግዚአብሔር ወኪል ነበር—2 ቆሮ. 1፥3-4፣ 12፤ 11፥2፤ 5፥20፦

1. በሐዋርያው ጳውሎስ ረጅም እና አሳዛኝ የእስር-ጉዞ ወቅት ሁሉ፣ ጌታ በዕርገቱ ጠበቀው፣ ከጭንቀት ክልል በላይ የሆነ ሕይወት እንዲኖርም አስቻለው—ሐዋ. 27፥13—28፥9፦
   ሀ. ይህ ሕይወት ሙሉ በሙሉ የተከበረ፣ ከፍተኛ የስብዕና ሰናይ ባሕርያት እጅግ የላቁትን መለኮታዊ ባሕርያት የሚገልጡበት፣ ከዓመታት በፊት ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ የኖረውን የሚመስል ሕይወት ነበር።
   ለ. ይህ ኢየሱስ በምድር ላይ በመለኮት በበለጠገው ስብዕናው እንደገና መኖሩ ነበር።
   ሐ. ይህ በወንጌላት የኖረው ድንቁ፣ የላቀው እና ምሥጢራዊው አምላክ-ሰው ከብልቶቹ በአንዱ በኩል በሐዋርያት ሥራ መኖር መቀጠሉ ነበር።
2. የአዲስ ኪዳን አማኞች እንደ የእግዚአብሔር ወኪሎች በማገልገል ከጳውሎስ ጋር አንድ አይነት መሆን ይችላሉ—1 ጢሞ. 1፥16።

## III. በእግዚአብሔር እንደተመረጡ፣ እንደተዋጁ እና ዳግም እንደተወለዱ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንደሆኑ፣ በእግዚአብሔር እንደተቀናበሩ፣ እግዚአብሔርን እንደሚኖሩ፣ እግዚአብሔርን እንደሚገልጡ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚንቀሳቀሱ እና እግዚአብሔርን እንደሚወክሉ ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ወኪል ማገልገል እንችላለን—ኤፌ. 1፥4-5፦

ሀ. በእግዚአብሔር እንደተመረጡ፣ እንደተዋጁ እና ዳግም እንደተወለዱ ሰዎች፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን አለብን—1 ቆሮ. 6፥17፦

1. የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መርህ እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ራሱን ከሰው ጋር አንድ እያደረገ እና ሰውን ከራሱ ጋር አንድ እያደረገ መሆኑ ነው—ዮሐ. 15፥4።
2. እግዚአብሔር መለኮታዊው ሕይወት እና የሰው ሕይወት አንድ ኑሮ ያለው አንድ ሕይወት ይሆኑ ዘንድ እንዲጋጠሙ ይሻል—1 ቆሮ. 6፥17።

ለ. በእግዚአብሔር መቀናበር ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥17፤ ቆላ. 3፥10-11፦

1. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ማንነታችን ከእርሱ ማንነት ጋር አንድ ቅንብር እንዲሆን በእርሱ ማንነት ይቀናበር ዘንድ ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ ማደል ነው—ኤፌ. 3፥17፤ 4፥4-6።
2. በመለኮታዊው ሕይወት እና በመለኮታዊው ሕይወት ሕግ መሥራት፣ እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን ይሠራል፣ እኛም በእርሱ ሕይወት እና ባሕርይ በእግዚአብሔር እንቀናበራለን—ሮሜ 8፥2፣ 6፣ 10-11፣ 29።

ሐ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንደሆኑ እና በእግዚአብሔር እንደተቀናበሩ ሰዎች፣ እግዚአብሔርን መኖር አለብን—ፊልጵ. 1፥21፦

1. በኢኮኖሚው መሠረት፣ የእግዚአብሔር ውጥን እኛ እንኖረው ዘንድ ንጥረ-ነገሩን፣ ይዘቱን እና የባሕርይውን ስሪቶች ወደ ማንነታችን ውስጥ ማስተላለፍ ነው—ሮሜ 8፥2፣ 6፣ 10-11።
2. የየዕለት ሕይወታችን እግዚአብሔር ራሱ መሆን አለበት፣ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ የመኖር ሕይወት መሆን አለበት—1 ተሰ. 2፥12፤ 1 ቆሮ. 10፥31።

መ. እግዚአብሔርን መግለጥ አለብን—ዘፍ. 1፡26፤ 2 ቆሮ. 3፡18፤ ሮሜ 8፡29፤ ቆላ. 3፡10፡-

1. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ እንገልጠው ዘንድ ራሱን እንደ ሕይወታችን ወደ ውስጣችን መሥራት ነው—ኤፌ. 1:11; 3:11; 2 ጢሞ. 1፡9።
2. እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ያለው ግብ ከእርሱ ጋር አንድ እንድንሆን እና ብዙዎች ለተካተቱበት መገለጡ እንኖረው ዘንድ ነው—1 ቆሮ. 6፡17፤ ፊልጵ. 1፡21፤ ኤፌ. 1፡22-23።

ሠ. እግዚአብሔርን እንደሚገልጡ ሰዎች፣ ከእግዚአብሔር ጋር መንቀሳቀስ አለብን—ኢያ. 1፡1-9፤ 6፡1-16፡-

1. እግዚአብሔር እንደ ታላቁ መንኩራኩር በኢኮኖሚው ባለው እንቅስቃሴው የእስራኤል ልጆች ከእርሱ ጋር እንዲተባበሩ አስፈልጎት ነበር—1፡1-9፤ 6፡1-16፡-
2. በልቡ መሻት እና በምድር ላይ ባለው እንቅስቃሴው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—ኤፌ. 1፡5፣ 9፤ ራእ. 14፡1-4።

ረ. ከእግዚአብሔር ጋር ስንንቀሳቀስ ሳለን፣ እግዚአብሔርን መወከል አለብን—ዘፍ. 1፡26-28፡-

1. እግዘአብሔርን በሥልጣን ለመወከል፣ እግዚአብሔርን በሕይወት መግለጥ አለብን፤ አሮን እግዚአብሔርን ለመግለጥ የትንሣኤው ሕይወት ስለነበረው፣ እግዚአብሔርን ለመወከል ሥልጣን ነበረው—ዘጸ. ቁ. 26፤ 2፡9፤ ዘኍ. 17፡1-8።
2. ለእግዚአብሔር ለመሥራት ተገቢው መንገድ እግዚአብሔርን መወከል ነው—ዘጸ. 7፡1-2።

ሸ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ከሆንን፣ በእግዚአብሔር ከተቀናበርን፣ እግዚአብሔርን ከኖርን፣ እግዚአብሔርን ከገለጥን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ከተንቀሳቀስን እና እግዚአብሔርን ከወከልን፣ እንደ እግዚአብሔር ወኪል ማገልገል እንችላለን፡-

1. እግዚአብሔር ኢኮኖሚውን ለማከናወን በሕይወት፣ በባሕርይ፣ በመገለጥ እና በአገልግሎት ከእርሱ ጋር አንድ አይነት ሊያደርገን ይችላል—ቆላ. 3፡4፤ 2 ጴጥ. 1፡4፤ ኤፌ. 3፡9።
2. ነቢዩ ኤልሳዕ በአገልግሎቱ እንደ እግዚአብሔር ሰው፣ በባህሪው እንደ እግዚአብሔር ወኪል ተመላለሰ፤ ዛሬም በክርስቶስ የምናምን እኛ በኢኮኖሚው እንደዚሁ እንደ እግዚአብሔር ወኪል የምናገለግል መሆን እንችላለን—2 ነገ. 4፡9፤ 1 ጢሞ. 6፡11፤ 2 ጢሞ. 3፡17።

*© 2022 Living Stream Ministry*